# ቁራሽ የናቀ ጠሙን ያድራል

በሰኔ ወር መጨረሻ የትምህርት ውጤት ማስረጃ/መረጃ መቀበያ ቀን፡፡

በልጅ፥ በአባትና በአጎት መካከል የተደረገ ጭውውት ከደብረ ብርሃን አካባቢ ከሚገኝ

አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱ፡፡

ዕለቱ ማክሰኞ ሰኔ ሠላሳ ነው፡፡ ተማሪዎች በዕለቱ ትምህርት ቤታቸው ሄደው የትምህርት መረጃቸውን እንዲወስዱ ተነግሯቸዋል፡፡ ልክ በዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ተማሪዎች መጡና ግቢውን ሞሉት፡፡ ወዲያውኑ የክፍል ኃላፊዎች በየክፍሉ ገብተው እንደ ውጤታቸው በማዕረግ ያለፉትን አንደኛ፥ ሁለተኛ እና ሦስተኛ የወጡትን ሲነገር ጭብጨባ በጭብጨባ ሆነ፡፡ ከበደም የስድስተኛ ሀ ተማሪ ከክፍሉ አንደኛ በመውጣቱ ተደስቶ ወዲያውኑ ውጤቱን ለማሳየት ወደ ቤቱ ሮጠ፡፡ እንደ ደረሰም አባቱን ያገኛል፡፡

ልጅ - አባባ ዛሬ ባገኘሁት የፈተና ውጤት እንደምትደሰት አልጠራጠርም!

አባት - ትደሰታለህ ነው? ወይስ እልል በቅምጤ ትላለህ ነው?!

ልጅ - መቼም ትሸልመኛለህ!

አባት - ሽልማት ብቻውን ምን ይፈይዳል? ስንተኛ ወጣህ ሁሉስ ላንድ ልጄ አይደል?

ልጅ - መጀመሪያ ያልኩህን ፈጽምልኝ እንጂ!

አባት - በዱቤ ነው እንዴ የምሸልምህ? ንገረኝ ወይም አሳየኝ፡፡

ልጅ - እንካ የምስክር ወረቀቴን! አንደኛ ነው የወጣሁት፡፡

አባት - ና ወደ እኔ ልሳምህ! ቀዩዋን ጊደር ለጉልማህ ሰጥቼሃለሁ! ብትወልድም ብትከብድም ላንተ ትሁን፡፡

(በመሃሉ ያባት ታናሽ ወንድም ማለት የከበደ አጎት ከተፍ ይላሉ)

አጎት - ምን ያሳስማችኋል? ምን አግኝታችሁ ነው?

አባት - ልጄ አንደኛ ወጣ እኮ! ሊቅ ሆነልን፡፡

አጎት - ይሄ ነው! አንዱ በቃኝ! የኔ ሺህ መክት! ና ሳመኝ!

ልጅ - አጎቴ! አንተስ ምን ትሸልመኛለህ?

አጎት - ታውቀው የለ! ነጩን ጥጃ ወይፈኑን ሰጥቼሃለሁ፡፡

ልጅ - አልፈልግም አባባ! ጊደር፣ አጎቴ ወይፈን ትላላችሁ፣ ምን ያደርጉልኛል? ይልቁንም ሁለታችሁም ሽጣችሁ አዲስ አበባን አሳዩኝ!

ያኔ ነው የሚማርከኝ እኔን!

አባት - የልጅ ነገር! ቦታውን አይረሳ! አዲስ አበባን ነገ ተነገ ወዲያ በራስህ
በትምህርትህ ትደርስበታለህ፤ የትም አይሄድም! ይሻላል የተሰጠህን ብትቀበልና
ብትጠቀምበት፤ “ቁራሽ የናቀ ጦሙን ያድራል ” ይባላልና ወይም
“ብልጥ ልጅ የሰጡትን እየበላ ያለቅሳል” የሚባለውንስ ሰምተህ አታውቅም?

አጎት - (ቀጠል ያደርግና) መቼም ልጅ የብልጠቱን ያህል ብስለት የለውም፥
ካሁኑ የግል ሀብት ማፍራት ማለት እኮ ሀብት የማካበት/የመያዝ እርሾ ነው።

ልጅ - ምን ያደርግልኛል ሀብት?

አጎት - እውነትም የልጅ ነገር! ከበርቴ፥ ባለፀጋ፥ ሀብታም የሚኮነው እኮ ሀብት በትንሽ
በትንሹ አጠራቅሞ ነው እንጂ/እኮ፤ አለበለዚያ ድሃ ሆነህ ስታክ ትኖራለህ!
የትምህርትም አንዱ ጥቅም ይህ ነው እኮ! የተሻለ ኑሮ ለመኖር።

ልጅ - ታዲያ አዲሰ አበባን ሳላይ ልቀር ነው?

አጎት - ከሁለት ዓመት በኋላ ስምንተኛ ክፍል ስትጨርስ/ስታልፍ ወደ ዘጠነኛ ክፍል
ስትዛወር ማለት ነው የግድ አዲስ አበባ ትሄድ የለ?! አንተ በርታና እለፍ እንጂ
አዲሰ አበባን ትንፈላሰስባታለህ!

ልጅ - አሁን ገና ገባኝ! እሺ! እሺ! አጎቴ! መቶ በመቶ ባላመጣ ደግሞ እኔ አይደለሁም!

አጎት - መቶ ደግሞ ምንድን ነው?

ልጅ - ፈተናዋን ድፍን አድርጎ ማግኘት ነዋ!

አጎት - ሙሉውን ማለት ነው?

ልጅ - ታዲያስ! መጠርጠሩስ?!

አባት - (ጣልቃ ገቡና) እግዜር ይባርክህ ልጄ! መጨረሻውን ያሳምርልህ!